# ክራር፣ ሰንጎ-መገን ፩



ሰምቶ ዘፈን ስልቱን
ክራር ሰንጎ-መገን
ተመልክቶ ልብሱን
በሴት መታጀቡን
ያን የድኻ ወገን
አንቆ ማጅራቱን
ነጠቀው ክራሩን…



በቅናት ተወጣጥሮ፣
አምባጓሮ፣ ጥል ፈጥሮ
ክራሩንም ከርክሮ
ሞክሮ፣ ተከራክሮ
አልሆን ሲለው ወርውሮ
ከወንዙ አሽቀንጥሮ
ሸፍቶ ገባ አጋሮ…



ምኑንም ያልዋለበት
ፍጹም ያልታደለበት
ቅኝቱን ላያውቅበት
ክራሩን ወሰደበት
ሰባብሮ ጣለበት
ከወንዙም ከተተበት
አፈር፣ ጠኔ ይብላበት!



ማ'ይሙት እስቲ አሁን
ምን ሊጠቅመው ይሆን
ድምፅ ያላደለውን
ደግሞ ዘፈን ሊዘፍን!
ሰው ቀብሮ ነው ማመን
ክራር፣ ሰንጎ-መገን…
አንጀት ማረር፣ መብገን።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

## ***ክራር፣ ሰንኅ-መገን ፪***



ከባሮ ወደ ቡልጋ፣
ከየጁ ወደ ጭልጋ
ሲዞር የሽፍታ ዋጋ
ሌሊት ተኝቶ ባልጋ
ከቆንጆ ጋ’ ሲያወጋ
ቦሊስ የደፋ ፋጋ
ተኩስ ከፍቶ ሲዋጋ



ተመታና ቀኝ እጁ
ጥቅልል አለ ከደጁ።
በእግዚሄር ሲፈረጁ
ተንከሎል እያቀናጁ
ተኝተው ሲያንጐላጁ
አንዱንም ሳያበጁ
ሞት ከተፍ ሳያረጁ…



በስሙ-አብ! ምን ነበር
በሰላምስ ቢኖር?
መጨረሻው ላያምር
እንዲህ ሆኖ ሊቀር!
እጁን አስረው ጠፍር
ተበተክስያኑ አጥር
ቸነከሩት በጦር…



መቀጣጫም ብለው
ተሳላሚ እንዲያየው
ከዋርካው ላይ ሰቅለው
ሦስት ቀኑ ሞላው፣
ባ’ራተኛ አውርደው
ለጂብና አሞራው
ጣሉት ከበረኻው።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

[Back to Meskot](#)

---

***The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by [Meskot](#). You may contact G.E. Gorfu for comments at [gegorfu@yahoo.com](mailto:gegorfu@yahoo.com).***